# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር

## ሁኔታ ግምገማ እና

## ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

## ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2022
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**

ርዕስ ........ i
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ 1
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 2
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 3
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝና ብመጠን ........ 4
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 4
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ........ 5
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 5
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 5
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ........ 6
እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 6
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ 6
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ........ 7
ሁኔታ አዝማሚያ ........ 7
ከዲሴምበር 11-20 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 7
ከዲሴምበር 11-20 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ ........ 7
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 8
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 9


# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በዲሴምበር የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛው፣ የምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተዘወትሮባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የለሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ ከዕለት ወደ ዕለት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ጨምሮ የተስተዋለ ሲሆንና በአንዳንድ የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቅዝቃዜው መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል። ለአብነት ያህል በደብረብርሀን -0.8፣ 1.4፣ 4.2፣ 3.6፣ 3.2፣ 4.8 እና 3.0 ፤በሐሮማያ 0.6፣ 0.2፣ 2.0፣ 1.8፣ 2.4፣ 1.0፣ 1.8፣ 1.8 እና 2.4፤ በቡኢ 4.0፣ 3.0፣ 4.0፣ 4.5፣ 4.0፣ 4.6 እና 4.0 ፤በጨፋ 2.4፣ 2.8፣ 3.0፣ 2.4፣ 3.2፣ 2.4፣ 3.4፣ 3.6፣ 4.8 እና 4.2፤ በአደሌ 4.0፣ 2.5፣ 2.2፣ 4 እና 4.5 ፤በመሐል ሜዳ 2.2፣ 2.8፣ 3.2፣ 4.5፣ 4.2፣ 4.8 እና 2.2 ፤አርሲ ሮቤ 4፣ 4.5፣ 4.5፣ 4፣ 4 እና 3.0፤ ዳንግላ 4.6፤ ደባርቅ 4.5፣ 4.5 እና 4.4፤ ደብረ ወርቅ 4.8 እና 4.8፤ጅማ 4.5 ፤ሮቤ 3.4፣ 3.6፣ 4.2 እና 4.4 ፤ነቅምት 1.0 ፤የትኖራ 4.1 እንዲሁም በወገል ጤና 4.5፣ 4.0፣ 4.0፣ 2፣ -0.2፣ 1.4፣ 2.6፣ 3.2፣ 2.6 እና 3.2 በዲግሪ ሴልሽየስ መመዝገቡን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ አካባቢዎች ከነበራቸው የደመና ሽፋን በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በጋምቤላ 40.9፣ በጂንካ 33.5፣ በማሻ 36.8 ፣ ሳውላ 51.0 እንዲሁም ጎሬ 35.0 በሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በጋምቤላ፤ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በኢሉአባቦራ፣ በባስኬቶ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በሞያሌ እንዲሁም በጥቂት የሲዳማ ዞኖች ላይ ከ5-68 ሚሜ የሚደርስ ከ2-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ በኢሉአባቦራ፣ በባስኬቶ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በሞያሌ እንዲሁም በቆራሂ ዞኖች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ የተቀሩት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3) ፡፡


ካርታ 1   ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3   ኢ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10 /2022 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር የመጀመሪያው አስር ቀናት የበጋው ደረቅየአየር ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተስተዋለ እንደነበር የተተነተኑ የአግሮ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ መኸር አብቃይ በሆኑት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው ደረቅ የአየር ሁኔታ በመካሄድ ላይ ላለው ሰብል ስብሰባ እና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳዉ ቅዝቃዜ በተለይም በሰሜን ምሥራቅ፣ የመካከለኛው፣ የምሥራቅ እና የደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አይሎ ነበር የተስተዋለዉ፡፡ በሌላ በኩል በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል። ይህም ሁኔታ በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበጋ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የተሻለ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር። በተጨማሪም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብ ኦሮሚያና የደቡብ ሶማሌ አካባቢዎች ከነበራቸው የደመና ሽፋን በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ መጠነኛ የሆነ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ይህም ሁኔታ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት በጎ ጎን ነበረው (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-10/2022 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር የመጀመርያው አስር ቀናት የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረውን ገፅታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በመካከለኛ እና በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛዉ እና መካከለኛው ባሮአኮቦ፣ በጥቂት በታችኛው ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት መካከለኛው ኦሞ ጊቤ እና የላይኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ከፍተኛ እርጥበት የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በአብዛኛው ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ነበራቸዉ (ካርታ 5)፡፡


ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 10/2022 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ ከምስራቅ አውሮፓ ወደ ሀገራችን በሚገባው ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በብዙ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚጎላበት ጊዜ ነው። በመሆኑም በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሌሊቱ እና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻራዊ ጥንካሬ ሊያሳይ ይችላል።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ በብዙ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ ከዚሁም ጋር በተያያዘ በተለይም በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሌላ በኩል ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሊአባቦራ፣ ሆረ ጉድሩ እና ምስራቅ ወለጋ፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ቤንች ማጂ እና ባስኬቶ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል፤ ከጋምቤላ ክልል የማጃንግ ዞን እና የአኙዋክ ዞን ምስራቃዊ አከባቢዎች ላይ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም የሰሜንና ደቡብ ወሎ ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት የደመና ሽፋን የሚኖራቸው ሲሆን፣ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ መጠነኛ ዝናብ እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ ሆነው ይቆያሉ።




ከዲሴምበር 11-20 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ከዲሴምበር 11-20 የሚኖረው ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲግሪ ሴልሺስ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በዲሴምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ ከማዘንበሉ ጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሰብል ስብሰባውና የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚካሄድበት ወቅት ነው፡፡ በሌላ በኩል ከደረቃማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የበጋው ወቅት የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በቀጣይነት የሚስተዋልበት ጊዜ ነው፡፡

በሚቀጥለው የዲሴምበር የሁለተኛዉ አሥር ቀናት የሚኖረው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን ቢኖረውም፤ ከደረቃማውና ከነፋሻማው አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ቅዝቃዜው በቀጣይነት እንደሚስታዋል የትንበያ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ባልጨረሱ ሰብሎች እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራት ለማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ፡፡ በሌላ በኩል በተለይም በምእራብና በደቡብ ምእራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የመፈጠር እድል ሊኖረው እንደሚችልና በተጨማሪም በሰሜንና በደቡብ ወሎ ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህም ሊገኝ የሚችለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 11-20/2022 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደረቃማው የአየር ሁኔታ በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት የሚኖረው ሲሆን፤ በሌላ በኩል በጥቂት በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ የሚገኙ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እረጥበት ሊኖራቸው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከነዚህም መካከል የላይኛው እና መካከለኛው ባሮአኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችናው ኦሞጊቤ፣ የስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በጥቂት የመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚያገኙ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች በአብዛኛዉ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቀዩ ይጠበቃል፡፡